| | |
|---|---|
| ዐይነት ፤ | ዐምደኛ ፡ ጽሑፍ ፤ "ብሔረ ፡ ጥበብ ። " |
| ርእስ ፤ | "ምድርና ፡ ኀዋ ።<br>ክፍል ፡ 4 ፤ ከርሠ ፡ ምድር ። " |
| ደራሲ ፤ | "ሥልጡንሕዝብና" ፡ መዜንው ። |
| ዕለት ፤ | መስከረም ፡ 2012 ፡ ዓ.ም. ። |
| ዝግጅት ፤ | ፍጹም ። |
| መጽሔት ፤ | "ሥልጡንሕዝብና" ፡ መዜንው ፥ ቍ.2012-001 ። |
| ማስታወሻ ፤ | |
| ማሳሰቢያ ፤ | |


**ብሔረ ፡ ጥበብ ።**

**Universe of Science | Univers de la science**

# ምድርና ፡ ኀዋ ።

## ክፍል ፡ 4 ፤ አራቱ ፡ ብሬቶች ።

ከመስከረም ፡ 1 ፡ ቀን ፡ አንሥተን ፡ በምንቈጥረው ፡ የምድራችን ፡ የ 365 ፡ ከ 1/4 ፡ ቀናት ፡ የፀሓይ ፡ ዙሪያ ፡ ዑደት ፥ አራት ፡ ብሬቶች ፡ (seasons) ፡ እኩል ፡ ለእኩል ፡ በተከፈሉ ፡ የ 91 ፡ ቀናት ፡ ወቅቶች ፡ የአየሯን ፡ ጠባይና ፡ የዕፀዋትዋን ፡ ልምላሜ ፡ ይለዋውጡታል ።

ምድራችን ፡ እንደ ፡ ዕንዝርት ፡ በራሷ ፡ ላይ ፡ እየተሽከረከረች ፥ በማይለወጠው ፡ ምሕዋሯ ፡ በፀሓይ ፡ ዙሪያ ፡ እንዲህ ፡ ስታውድ ፥ ወዳንድ ፡ ወገን ፡ ጋደል ፡ ባለው ፡ አቋሟ ፡ ምክንያት ፡ ባንድ ፡ ወቅት ፡ ደቡባዊው ፡ ንፍቀ-ክበቧ ፡ ለፀሓይ ፡ ቀርቦ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፥ ሞቃት ፡ ወራትን ፡ ያገኛል ፤ እንደዚሁ ፥ ለፀሓይ ፡ የራቀው ፡ ንፍቀ-ክበቧ ፡ ቀዝቃዛ ፡ ወራትን ፡ ያገኛል ። ስለዚህ ፥ አደቡባዊው ፡ ንፍቀ-ክበብ ፡ በጋ ፡ ሲኾን ፥ አሰሜናዊው ፡ ንፍቀ-ክበብ ፡ ደግሞ ፡ ክረምት ፡ ይኾናል ። ብርሃንና ፡ ጨለማውም ፡ እኩል ፡ ለእኩል ፡ 12 ፡ ሰዓት ፡ ከመኾን ፡ ይልቅ ፥ እንደ ፡ ንፍቀ-ክበቡ ፡ ወይ ፡ ወደ ፡ ጨለማው ፡ ወይ ፡ ወደ ፡ ብርሃኑ ፡ ያደላል ።

### ብሬቶች ።

እምድር ፡ ወገብጌ ፡ (equator) ፡ ያለው ፡ የምድራችን ፡ አካባቢ ፡ ኹሉ ፡ ባለኹለት ፡ ብሬቶች ፡ ነው ፡— ክረምትና ፡ በጋ ።

ከምድር ፡ ወገብጌ ፡ ወይ ፡ ወደ ፡ ደቡብ ፡ ወይ ፡ ወደ ሰሜን ፡ በራቅን ፡ መጠን ፡ ግን ፥ የብሬቱ ፡ መጠን ፡ ከ 2 ፡ ወደ ፡ 4 ፡ ያድጋል ። እነዚህ ፡ አራት ፡ ብሬቶች ፡—

- ***መፀው*** ፡ (መከር) ፥ ከመስከረም ፡ 27 ፡ እስከ ፡ ታኅሣሥ ፡ 26 ፤
- **ሐጋይ** ፡ (በጋ) ፥ ከታኅሣሥ ፡ 27 ፡ እስከ ፡ መጋቢት ፡ 26 ፤
- **ጸደይ** ፡ (በልግ) ፥ ከመጋቢት ፡ 27 ፡ እስከ ፡ ሠኔ ፡ 26 ፤
- **ክረምት** ፥ ከሠኔ ፡ 27 ፡ እስከ ፡ መስከረም ፡ 26 ።

እንደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ባሉ ፡ ሀገሮች ፥ ከወርኀ ፡ ጽጌ ፡ መስከረም ፡ ዠምሮ ፡ የሚታየው ፡ የ***መፀው*** ፡ ልምላሜና ፡ የአየር ፡ ልስላሴ ፥ በተለይ ፡ ይዘመርለታል ፤ በቀደመው ፡ ክረምት ፡ ታርሶ ፡ የተዘራውም ፡ አዝመራ ፡ የሚደርስበት ፡ ወቅት ፡ ስለ ፡ ኾነ ፥ ዘመነ ፡ መከር ፡ ይባላል ።

**ሐጋይ** ፡ ወይም ፡ **በጋ** ፡ ደግሞ ፥ ዝናብ ፡ (ዝናም) ፡ የሚታጣበትና ፡ ምድር ፡ የምታጥጥበት ፡ ወቅት ፡ በመኾኑ ፥ ድርቅ ፡ ቢታይበትም ፥ በኢትዮጵያ ፡ አካባቢ ፥ በተለይ ፡ በደጋው ፡ ክፍል ፥ እጅግ ፡ ይበርዳል ።

**ጸደይ** ፡ ወይም ፡ **በልግ** ፥ መለስተኛ ፡ ዝናብ ፡ ስለሚዘንብበት ፥ ገበሬው ፡ የበልግ ፡ ዕርሻውን ፡ ዐርሶ ፡ ቶሎ ፡ የሚደርስ ፡ እኽሉንም ፡ ዘርቶ ፡ ያጭድበታል ።

በመጨረሻም ፥ የ**ክረምት** ፡ ወራት ፡ ኀይለኛ ፡ ዝናብ ፡ የሚዘንብበት ፣ ወንዞች ፡ የሚሞሉበት ፣ ምድሩ ፡ ኹሉ ፡ የሚደፈጭበት ፡ ወቅት ፡ በመኾኑ ፥ ካገር ፡ ወዳገር ፣ ከገበያ ፡ ወደ ፡ ገበያ ፡ መዘዋወር ፡ ቀርቶ ፥ ገበሬው ፡ በያለበት ፡ ዕርሻውን ፡ በማረስ ፣ በማለስለስና ፡ በመዝራት ፥ ከዚያም ፡ በማረም ፡ ተጠምዶ ፡ ይከርምበታል ❖


©ኢ..ሀ.ሥ.አ. ፥ 2012 ፡ ዓ.ም. ።